ከአዲስ ፕሬስ ጋዜጣ የመጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም
እትም የተወሰደ



አዲስ ፕሬስ መጋቢት 28 ቀን 2002 ዓ.ም.

እልፍኝ

«ኢህአዴግን ጥላሸት የቀባው የራሱ ታሪክ ነው»

አቶ አንዱዓለም አራጌ
የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ዋና ፀሐፊ

> ብርቱካን ታማለች፡፡ በጣም ታማለች፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ እሷም ይሄን ባልተናገረች፤ እኛም ጉዳዩን ለህዝብ ይፋ ባላደረግን ነበር፡፡

«ኢህአዴግን ጥላሸት ...

--- ከገፅ 5 የዞረ

ምክንያቱም በሬዲዮና በቴሌቪዥን ብዙ አድማጭ፣ ብዙ ተመልካች ስለሚኖር ይሄ ነገር ከተላለፈ ኢህአዴግ ምን ያህል ህገ ወጥ እንደሆነ በተጨባጭ ማስረጃ የሚያሳይ እንደሆነ ስለሚያውቁ፤ ቆርጠው አጠፉት።

አዲስ ፕሬስ፡- ከወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ጋር በተገናኘ በአሁኑ ወቅት የጤና ሁኔታቸው አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደደረሰ የተለያዩ የውጭ ሀገር የሰብአዊ መብት ሪፖርተሮች እየገለፁ ነው። የእናንተ ፓርቲም የጤናዋን አሳሳቢነት በሚመለከት መግለጫ አውጥቷል። መንግስት ግን ምንም የተፈጠረ ነገር የለም፤ ይልቁንም የወ/ሪት ብርቱካንን ጉዳይ የፖለቲካ አጀንዳ ለማድረግ እየተሞከረ ነው፤ የሚል ምላሽ እየሰጠ ነው። በዚህ ላይ ማብራሪያ ቢሰጡን?

አቶ አንዱአለም፡- ብርቱካን ታማለች። በጣም ታማለች። ያ ባይሆን ኖሮ እኛም ይሄን ባልተናገርን! እኛም ጉዳዩን ለህዝብ ይፋ ባላደረግን ነበር። ብርቱካንን በደንብ እናውቃታለን። በመከራም ጊዜ የጸናች ሰው ነች። ለይስሙላ ብላ የምታደርገው ነገር የላትም። እሷን ከወንዶቹ የሚለያት በፈተና ወቅትም እንኳን አለመንበርከኳና ሀቁን ለመናገር ወደኋላ አለማለቷ ነው። ስለዚህ የተናገርነው እውነት ነው። ያለችው በመከራ ውስጥ ነው። ያ መከራ ሳያንሳት ደግሞ በአስጊ ሁኔታ ታማለች። ተገቢውን ህክምና ግን እየሰጧት አይደለም። ስለዚህ የኢህአዴግ ውሸት በእሷ ላይ የተጀመረ ሳይሆን ለአስራ ዘጠኝ አመት የዘለቀ ውሸት ቀጣይ ነው። ኢህአዴግ ስልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ! አንድም ቀን በሰብአዊ መብት ተቋማት ያልተወቀሰበት ጊዜ የለም። አንድም ቀን በነፃ ፕሬስ ተሟጋቾች አካላት ያልተወቀሰበት! ያልተወገዘበት አመት ኖሮ አያውቅም። እሱም አንድም ቀን ጥፋቱን ተቀብሎ አያውቅም። ሁሌጊዜም መፈረጅ ነው የሚቀናው። ሁልጊዜ ከተጠየቀው ሌላ እሱ ሌላ ማለት ነው የሚቀናው። እንጂ ሰዎች ጥፋቱን አውቀው ሲነግሩት ተሸማቆ ለመስተካከል ጥረት የሚያደርግ ፓርቲ አይደለም። ኢህአዴግ ከእለት እለት እየታረመ የሚሄድ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ አምባገነን እየሆነ የሚሄድ ፓርቲ ነው።

አዲስ ፕሬስ፡- እናንተ ወ/ሪት ብርቱካንን መጠየቅ እንዳልቻላችሁ ገልፃችኋል። ምናልባት ከእናንተ ውጪ የሚንቀሳቀሱ እንደ ፕሪዝን ፌሎሺፕ አይነት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ከዚህ በፊት የሽምግልና ተግባር ሲፈፅሙ ከነበሩ አካላት የሰማችሁት ነገር ካለ ቢገልፁልን?

አቶ አንዱአለም፡- ቀደም ሲል አንድ ጊዜ የፕሪዝን ፌሎሺፕ ሰዎች እንደጎበኟት ሰምተናል። ግን ይሄ በጣም ቆይቷል። አሁን ያለችበትን ሁኔታ ግን ሄደው አላዩም። ሌላው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በጭራሽ ድርሽ ብለው አያውቁም። በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች? በምን ሁኔታ እንደምትኖርና ስለጤናዋ ሁኔታም ለማየት አልቻሉም። እነሱን እንኳ ትተን ቀደም ሲል የሽምግልና ስራ ሲሰሩ የነበሩት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ እንኳን ለማየት የሚችሉ አልመሰለኝም። እሳቸውም አልጠየቋትም። እሳቸው በዚህ ረገድ የተሻለ እድል ነበራቸው። ሆኖም ብርቱካንን እንዳያዩዋት ተደርጓል። ይህም እሷ ላይ በተለየ ሁኔታ ያለውን ጫና የሚያሳይ ነው። የሆነ ሆኖ እኛ ሁሉንም ህጋዊ ተብለው የተቀመጡ አማራጮች እንጠቀምባቸዋለን። ሌሎ የምንማፀንባቸውን በሮች ሁሉ እያንኳኳን እንገፋበታለን።

አዲስ ፕሬስ፡- የእነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና የአቶ ስዬ አብርሃ ወደ እናንተ ፓርቲ መግባት ፓርቲያችሁን ምን ያህል አጠናክሮታል?

አቶ አንዱአለም፡- የነዚህ ሰዎች ወደ ፓርቲው መግባት ከፍተኛ ጥቅም አምጥቷል። ለምሳሌ ከተለያዩ ወገኖች ጋር ማሰባሰብ አስችሏል። ፓርቲ ውስጥም በሚገኙባቸው ኃላፊነቶች በጣም ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረጉ እንዳሉ በርግጠኝነት መናገር እችላለሁ። አባላቶቻችንና ደጋፊዎቻችን እንዲሁም ሌላውም ህዝብ ከውጪም ሆነ ከሀገር ውስጥ እነሱ ወደ እኛ ፓርቲ በመግባታቸው ደስታቸውን እየገለፁ ነው። ከሀገር ውስጥ ለፓርቲያችን ተጨማሪ ደጋፊዎችን እያስገኙልን መሆኑን ለመረዳት እነሱ በሚገኙባቸው ስብሰባዎች ላይ ያለውን የህዝብ ድጋፍ ማየት በቂ ነው። ስለዚህ እኔ በእውነቱ ለፓርቲያችን ተጨማሪ ድጋፍ እያመጡ እንደሆነና ፓርቲያችንን እያጠናከሩት እንደሆነ እረዳለሁ።

አዲስ ፕሬስ፡- መድረክን አስመልክቶ አስተያየት የሚሰጡ አንዳንድ ወገኖች መድረክ ከቀድሞ ቅንጅት አንፃር ሲታይ የመፈረካከስ እድሉ የሰፋ ነው ይላሉ። እርስዎስ ምን ያህል ያሰጋዎታል?

አቶ አንዱአለም፡- እንግዲህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲመሰረቱ የየራሳቸው እሳቤዎች አሏቸው። ለምሳሌ በ97 ቅንጅት ሲመሰረት የራሱ እሳቤዎች ነበሩት። ሆኖም ብዙ ያላሰብናቸውና ይከሰታሉ ያላልናቸው ነገሮች ሲከሰቱ አይተናል። ደግሞ ሁልጊዜ ከአንድ ነገር ውድቀት በኋላ መማማር ይጠበቅብናል። አሁን እኛ በቅንጅት ውስጥ ከተፈጠረው ስህተት የሚገባንን ያህል ለመማር ጥረት እያደረግን ነው። መድረክ በኢትዮጵያ ሁነኛ የፖለቲካ ሀይል ሆኖ መውጣትም የሆነ የፖለቲካ መደላድል እንዲመጣ ያግዛል። በመሆኑም ይፈረካከሳል የሚለው አስተያየት ተጨባጭነት ያለው አይመስለኝም። ምንግዜም ሁለትም ሦስትም ሀይሎች ያሉበት ነገር አብሮ ካለ ልዩነት ይኖራል። ይሄ ተፈጥሮአዊ ነው። እንኳን በፓርቲ ደረጃና በግለሰብ ደረጃም ልዩነት ይኖራል። የሙታን ስብስብ እስካልሆነ ድረስ። ምናልባት እንደ ኢህአዴግ አይነቱ ፓርቲ ውስጥ ልዩነቶች ላይኖሩ ይችላሉ። ሆኖም በዲሞክራሲያዊ ስብስብ ውስጥ ግን የልዩነቶች መኖር አያስገርምም። ዋናው የሚያስፈልገውም በውስጥ ያሉ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን ፈትቶ ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያደርሱ ሽግግሮች ነው። ይሄን በመድረክ ማየት ይቻላል። የመድረክ ጠንካራ ጎን ይሄ ነው። ከአሁን በኋላም በድክመቶቻችን ላይ የበለጠ እየሰራን እንሄዳለን።

አዲስ ፕሬስ፡- መድረክ በኢትዮጵያ የተቃዋሚዎች ትግል ላይ ምን አይነት እሴት ጨምሯል?

አቶ አንዱአለም፡- መድረክ ከኢህአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ አንፃር እንደ መድሃኒት የሚሆን ስራ እየሰራ ነው። በቅንጅት መፍረስ አንገቱን ደፍቶ የነበረው ህዝብም አሁን መነቃቃቱንና ወደ ትግሉ መመለስ ጀምሯል። ይሄ የሆነው በመድረክ መፈጠር ነው። መድረክ ከመጣ ወዲህ በየቀኑ በአባልነት የሚመዘገበው ሰው ቁጥር ጨምሯል። ከዚህ በላይ ግን መድረክ ወደፊት ሊሰራው የሚችለውና ሊያመጣው የሚችለው እድል ነው ትልቁ ነገር።

አዲስ ፕሬስ፡- መድረክ የሰነቀውን ተስፋ እውን ለማድረግ ምን ያህል ህዝቡ ውስጥ እየደረሰ ነው?

አቶ አንዱአለም፡- ለአባሎቻችን የሚያስፈልጉ ግብአቶችን እያቀረብን ነው። አመራሮቻችን በየምርጫ ጣቢያው ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ነው። የተለያዩ ህዝባዊ ስብሰባዎችንም እያካሄድን ነው። በተቻለን መጠን ህዝቡ ጋር ወርደን እየሰራን እንገኛለን።

አዲስ ፕሬስ፡- ኢህአዴግ መድረክንና ሌሎች ተቃዋሚዎችን የተሰሩ ስራዎችን የማያደንቁና ጥላሸት መቀባት ብቻ ነው የሚያውቁት፤ ሲል ይደመጣል። በርግጥ ኢህአዴግ የሰራውን ጥላሸት እየቀባችሁ ነው?

አቶ አንዱአለም፡- ብረት ምጣድን እንዴት አድርገህ ጥላሸት ትቀባዋለህ? ብረት ምጣድ በራሱ ጥቁር ነው። ኢህአዴግም እንደዛው ነው። እኛ ሳንቀባው እራሱ «ጥቁር» ነው። ኢህአዴግን ጥላሸት የቀባው የራሱ ታሪክ ነው። የራሱ የፖለቲካ ባህል ነው። ወርክሾፕ ወቅት ይሄንን በተደጋጋሚ ጠቅሰናል። ስለዚህ ኢህአዴግ ጥላሸት የሚቀባው ማንንም የለውም። የራሱ ታሪክ ጥላሸት ቀብቶታል። እራሱን በራሱ ጥላሸት ሲቀባ የኖረ ድርጅት ነው። ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ የኖረ ድርጅት ነው። ያንኑ የሆነውን ደግመን ከመናገር ያለፈ ነገር አላደረግንም። እኔ ስለ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዝብ የማያውቀውን ነገር እየነገርኩ ነው ብዬ አላስብም። እንደውም እኛ ከምንናገረው በላይ ስለ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ያውቃል። በየሰፈሩ በየስራ ቦታው በካድሬዎች የሚደርስበትን እንግልት ያውቀዋል። ስለዚህ ኢህአዴግ አሁንም የጨለመ ገፅታ ነው ያለው። እና ኢህአዴግን ጥላሸት መቀባት አያስፈልገውም።

አዲስ ፕሬስ፡- ከአዲሱ የምርጫ ቦርድ የጋዜጠኞች ስነምግባር ደንብና የቪ.ኦ.ኤ. ፕሮግራሞች እንዳይሰራጩ ከመከልከሉ ጋር ተያይዞ ህዝቡ በቂና አስተማማኝ መረጃ ሊያገኝ የሚችልበት መንገድ አለ ትላላችሁ?

አቶ አንዱአለም፡- የህገ መንግስቱ አንቀፅ 29 ቅድመ ምርመራን ይከለክላል። ሆኖም አሁን እንደሚታየው፣ ህዝቡ ስለምርጫው በቂ መረጃ እንዳያገኝ የተለያዩ ክልከላዎች እየተደረጉበት ነው። ህገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ መሆኑ ሲገባው ኢህአዴግ እንደሚመቸው የሚያወጣቸው ህጎች፣ ደንቦችና ትዕዛዞች የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥሱ ናቸው። ቪ.ኦ.ኤንም በተመለከተ የሚያሳፍር ነገር ነው ኢህአዴግ ያደረገው። ቀደም ሲል በምንናገረው በምንፅፈው ላይ ገደብ ተደርጎብን ነበር። አሁን የምንሰማውንም ሊመርጥልን እየከጀለ ነው። ኢህአዴግ ነጻ ሆነን የመናገር፣ ነጻ ሆነን የመፃፍ፣ የመስማት ነገር የሚደነግጉ ሰብአዊ መብቶቻችንን እየነጠቀን ነው። እንደ ሰው በነፃ ካልተናገርን፣ ካልፃፍን፣ የፈለግነውን ካላዳመጥን መረጃ የማግኘት መብቶቻችንን ከማጣጣም በተቃራኒ እንደ ግኡዝ እየተቆጠርን ነው። ግብሩን ነው እንደዚህ የምንከፍለው። ለምሳሌ በምርጫ ክርክሮች ቅድመ ምርመራ እየተደረገ የሚቆረጡ ሀሳቦች አሉ። እኛ የተከራከርንበትን ሀሳብ እንደፈለገ የሚያስቆራርጠው ኢህአዴግ ነው። በዚህ ሁኔታ ህዝቡ በቂ መረጃ አገኘ ነው ማለት አይቻልም። እንደ የኢህአዴግ ጋዜጠኛ ይሄ ነገር ያስከስሳል ይሉና ያለ ከልካይ የፈለጉትን ሀሳብ ይቆራርጡሃል። ለነገሩ የኛ ሀሳብ የተቆረጠው በጋዜጠኞች ብቻ ሳይሆን በኢህአዴግና በኢ.ዴ.ፓም ትብብር ነው።

አዲስ ፕሬስ፡- አንዳንድ ወገኖች «ተቃዋሚዎች ውጤቱ ቀድሞ በታወቀ ምርጫ ላይ ገብ ብለው ነው አሳታፊ መስፈርትን የሚያሟሉት» ይላሉ። ለማስረጃነትም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በቅርቡ ለፓርላማ በአንዳንድ ተቃዋሚዎች ላይ ከምርጫው በኋላ እርምጃ እንወስዳለን የሚል ቃና ያለውን ንግግር ማቅረባቸውን ይጠቅሳሉ። እናንተ ውጤቱ በታወቀ ምርጫ እየተሳተፋችሁ እንዳላችሁ ይሰማችኋል?

አቶ አንዱአለም፡- ይሄ በህዝብ ትግል ላይ ነው የሚመሰረተው። ህዝቡ ከታገለ ማሸነፍ ይቻላል። ህዝቡ ከተባበረ አንድም ምድራዊ ሀይል ሊያሸንፈው አይችልም። ሆኖም ህዝቡ በኢህአዴግ ተማርሮ! በኢህአዴግ ብዙ ተሸውዶ ተስፋ ቆርጦ ቤቱ የሚቀመጥ ከሆነ! ኢህአዴግ እንደለመደው የህዝቡን ድምፅ በጉልበት ይወስደዋል። ሆኖም ህዝቡ ተስፋ ሳይቆርጥ ውስጡ ያለውን ሀይል ካሳየ ምርጫውን ማሸነፍ ይችላል። ምርጫ አራት ደረጃዎች አሉት። አንደኛው ለምርጫ መመዝገብ፣ ሁለተኛው መምረጥ፣ ሦስተኛው ድምፅን መጠበቅና አራተኛ የምርጫውን ቆጠራ በንቃት መከታተል ናቸው። እነዚህን አራት ደረጃዎች ህዝቡ ከፈጸመ፣ የህዝቡ ድምፅ የሚሸሸግበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ለምሳሌ ሀደያ ላይ የተሻለ ተሞክሮ አለ። ምርጫ መርጠው ብቻ ወደ ቤታቸው አይሄዱም። ድምፃቸው እስኪቆጠር ድረስ ይጠብቃሉ። ውጤቱ ከታየ በኋላ ነው ወደ ቤታቸው የሚሄዱት። ህዝቡ በዚህ መንገድ ተሰማርቶ የሚሰራ ከሆነ አይደለም ኢህአዴግን ሌላ የተሻለ ሀይልን መቋቋም ይችላል። ህዝቡ ካልተባበረ ግን ኢህአዴግም እንደሚያሸንፍ ሊያደርግ ይችላል።

አዲስ ፕሬስ፡- መድረክ ከዘንድሮው ምርጫ ምን ይጠብቃል?

አቶ አንዱአለም፡- ማሸነፍን።

አዲስ ፕሬስ፡- ቀረ የሚሉት ነገር ካለ ...

አቶ አንዱአለም፡- እንግዲህ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ያሉትን ነው መድገም የምፈልገው። መፍራት ካለብን መፍራት ያለብን ፍርሃትን እራሱን ነው እንጂ ኢህአዴግን መፍራት አይገባንም። በፈራነው ቁጥር አሁን ያለንበት የመከራ ዘመን ይረዝማል። ደፍረን በሰላማዊ መንገድ ተማምነን እጅ ለእጅ ተያይዘን በታገልን መጠን ደግሞ የመከራ ቀንበራችን የሚሰበርበት ጊዜ እያጠረ ይሄዳል። ስለዚህ አንዳችን አንዳችንን እየፈራራን እየተጠራጠርን ሳይሆን ተማምነን ለውጥ ማምጣት እንችላለን። የኢትዮጵያ ህዝብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ከመድረክ ጋር ሆኖ በመታገል፣ ፍርሃቱን አስወግዶ ለድል እንዲበቃ ያሉትን ቀናቶች በስፋት እንዲጠቀምባቸው ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

አዲስ ፕሬስ፡- እናመሰግናለን።

አቶ አንዱአለም፡- አመሰግናለሁ።